
# ጮክ ብሎ የማንበብ መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental
until every child reads




**ሞር ዛን ፒች (More Than Peach)**

*ደራሲ፣ ቤለን ዎዳርድ (Bellen Woodard)*

*ሰዓሊ፣ ፋኒ ሊየም (Fanny Liem)*

**ይዘቶች (Themes)፤ ማካተት** (Inclusion) አድቮኬሲ (Advocacy)፣ ችግር መፍታት (Problem-Solving)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** በእውነተኛ ታሪክ ላይ በመመስረት አንዲት ወጣት ልጅ "የቆዳ ቀለም (skin color)" ክሬኖች ከሁሉም ሰው ቆዳ ጋር እንደማይዛመዱ አስተውላለች እና ክፍሏን ለሁሉም ያካተተ ለማድረግ እርምጃ ወስዳለች!

## ጮክ ብለው ያንብቡ

**ከንባብ በፊት፤ ዳራ ይገንቡ (Build Background)**

- "ፍትሃዊ ያልሆነ ነገር አስተውለህ ታውቃለህ? ያንን ነገር በሚመለከት ምን አደረግህ?" በማለት ይጠይቁ
- ይህ ታሪክ ችግር አይታ ለማስተካከል ስለሰራች እውነተኛ ሴት ልጅ እንደሆነ ለልጅዎ ያስረዱት። ስናነብ፤ ምን እንደምታስተውል እና ለመርዳት ምን እንደምታደርግ አስብ

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ**

- ልጅቷ በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ "የቆዳ ቀለሞች (skin color) " ከለር ምን ታስተውላለች?
- ከለሩ (crayon) ከሁሉም ሰው ቆዳ ጋር እንደማይመሳሰል ስትረዳ ምን ይሰማታል?
- ችግሩን ለመፍታት ምን ለማድረግ ወሰነች?
- በድርጊቷ ምክንያት ምን ይለወጣል?

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- "ልጅቷ ስለ ክሬን ችግር መናገሯ ለምን አስፈላጊ ነበር? ተግባሯ ሌሎች ተማሪዎችን የረዳቸው እንዴት ነው?" በማለት ይጠይቁ።

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህንን መጽሃፍ ከወደደው፤**

- የ "ለውጥ ፈጣሪ (Change Maker)" ጆርናል (journal) ይጀምሩ። ልጅዎ በክፍላቸው፣ በቤታቸው ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ የበለጠ ፍትሃዊ ወይም አካታች የሆነ ነገር እንዲያውቅ እርዱት። በታሪኩ ውስጥ ያለችው ልጅ እንዳደረገው ሁሉ ስለችግሩ ይሳሉ ወይም ይፃፉ እና መፍትሄዎችን አንድ ላይ ይሰብስቡ።


©2026 Reading Is Fundamental